## የሕዝብ ቆጠራው ለDC አስፈላጊ ነው

**$6B**



የፌደራል መንግስት በየዓመቱ ለዲስትሪክቱ ወሳኝ የሆኑ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም እንዲረዳ፣ ዶላር በላይ ያከፋፍላል፡፡



የሕዝብ ቆጠራ የመረጃ ስብስብ፣ በዋርድ (Ward) እና ANC የክልል ወሰን ውስጥ፣ በዲስትሪክቱ ዙሪያ ያለውን የሕዝብ ብዛት እድገት እና እንቅስቃሴ፣ አዲስና የተሻሻለ መረጃ ለመስጠት የሚያገለግል ነው፡፡



በዲስትሪክቱ የሚገኙ ድርጅቶች፣ በከተማው ዙሪያ በሚደረጉ፣ የበጀት አያያዝ፣ እቅድ ማውጣት፣ እና የፖሊሲዎች ውሳኔ አሰጣጥ በሚያደርጉ ጊዜ፣ ትክክለኛ የሕዝብ ቆጠራ የመረጃ ስብስብ ላይ እምነታቸው ይጥላሉ፡፡

# የDC የልጆች ቆጠራ!

### የሕዝብ ቆጠራው በልጆች እና ትምህርት ቤቶች ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል

የፌደራል መንግስት፣ የሕዝብ ቆጠራ የመረጃ ስብስብን በመጠቀም፣ በDC ትምህርት ቤቶች ውስጥ በወሳኝነት አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች እና ፕሮግራሞች፣ በገንዘብ እርዳታ ለመደገፍ በየዓመቱ $128 ሚሊዮን ዶላር ይመድባል:

- ልዩ ትምህርት (Special education)
- በነፃ እና ቅናሽ ክፍያ ምሣ ማግኘት
- የክፍል መጠን መቀነስ
- የክፍል ውስጥ ቴክኖሎጂ
- የአስተማሪ ስልጠና
- ከትምህርት ክፍለጊዜ በኋላ (after-school) ፕሮግራሞች
- በቅድሚያ የተሰጠ (Head Start)





**እያንዳንዱ ልጅ አለመቆጠሩ፣ በDC ትምህርት ቤቶች የገንዘብ እርዳታ (fund) ላይ ኪሳራ ያመጣል፡፡**

**የሕዝብ ቆጠራ የመረጃ ስብስብ፣ ለማደጎ እንክብካቤ፣ SNAP፣ ሜዲኬድ እና የመኖሪያ ቫውቸሮች ላይ የፌደራል ገንዘብን ለመመደብም ያገለግላል፡፡**

እንዴት ለመሳተፍ እንደሚቻል የበለጠ መረጃ ለማግኘት: dccensus2020.dc.gov.

District of Columbia Office of Planning

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR



# የ2020 የሕዝብ ቆጠራ ይቆጠሩ

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## የሕዝብ ቆጠራ ምንድነው፤ መቼስ ነው የሚከናወነው?

የ2020 የሕዝብ ቆጠራ ጥቂት መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች የያዘ መጠይቅ ነው፡፡ በየ10 ዓመቱ፣ እያንዳንዱ በአሜሪካ አገር ውስጥ የሚኖር ሁሉ፣ እንዲያጠናቅቅ የሚጠየቅ፣ ቀላል የሆነ፤ ነገር ግን በጣም አስፈላጊ የሆነ የሕገ-መንግስት ተግባር: ለሕዝብ ቆጠራው ምላሽ ይስጡ፡፡

## የሕዝብ ቆጠራው ምንም ምን ዓይነት ጥያቄዎችን ይጠይቃል?

የ2020 የሕዝብ ቆጠራ ጥያቄዎች፤ ስለ ዕድሜ፣ ፆታ እና በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ፤ ልጆች እና አዲስ የተወለዱ ሕፃናትን ጨምሮ፣ የሚኖሩት ሰዎች ቁጥር የሚጠይቅ ነው፡፡ ቀጣዩ የአስር ዓመት የሕዝብ ቆጠራ በMarch 2020 ውስጥ የሚጀመር እና ምላሽን መስጠትም፤ ቀላል፣ ችግር የማይፈጥር፣ እና አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

## ቋሚ ነዋሪነት ሳይኖር፣ የሕዝብ ቆጠራ ቢሮው እንዴት ሕዝብን ይቆጥራል?

የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ ሰራተኞች፣ በቡድ የመኖሪያ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ፡ እነዚህም ማለት፤ በኮሌጅ ዶርም ውስጥ፣ በወታደራዊ ሰፈሮች ውስጥ፣ በነርሲን ሆም እና በመጠለያዎች ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን፣ በቤት አልባነት ወይም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የተፈናቀሉን ጨምሮ፤ በአካል በመገኘት ቆጠራውን ያካሂዳል፡፡ በ'መጋቢት 23 ቀን 2012' (April 1, 2020)፣ በጊዜያዊነት ከጓደኛ ወይም ከቤተሰብ ጋር የሚኖሩ፣ ቋሚ መኖሪያ የሌላቸው ልጆች እና ቤተሰቦች፣ በዚያ ባሉበት አድራሻ መቆጠር አለባቸው፡፡

## የሕዝብ ቆጠራ ምላሾች በሚስጥር ተጠብቀው ይያዛሉ?

ሕጉ በሚጠይቀው መሰረት፣ የሕዝብ ቆጠራ ቢሮው ሁሉንም መረጃዎች በሚስጥራዊነት መያዝ እና ምላሾቹን የስታትስቲክ መረጃዎች ለማዘጋጀት ብቻ ይጠቀምባቸዋል፡፡ ምላሽዎ ሙሉ ለሙሉ የተጠበቀ እና እርስዎን በሚጎዳ መልክ፣ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡ የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ ሰራተኞች የግል መረጃዎችዎን ለዘለዓለም ለመጠበቅ ማሕላ የገቡ እና ማንኛውም ሕግ መጣስ ከተከሰተ፣ እስከ $250,000 የገንዘብ ቅጣት እና/ወይም እስከ አምስት ዓመት የእስራት ቅጣት ያስከትላል፡፡